# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራያዊ ሪፐብሊክ

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴያትር

# የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት/2015

**አዲስ አበባ**

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራያዊ ሪፐብሊክ**

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴያትር**

**የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት**

የኢትዮጲያ ብሄራዊ ቴያትር የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጲያ ብሄራዊ ቴያትር ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የዋና ኦዲተሮች የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

**ኦዲታችን፡-**

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የኢትዮጲያ ብሄራዊ ቴያትር ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች ፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በቴያትር ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት ፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የኢትዮጲያ ብሄራዊ ቴያትር የ2014 የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

<u>ወጪ፤</u>

1. የፌደራል የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ዓ.ም አንቀጽ 12 ንዑስአንቀጽ 1 'ሀ' ለደመወዝ ዝግጅት የሚከተሉት መረጃዎች መሟላት አለባቸው በሚለው ውስጥ የሥራ ክፍሎች የክፍሉ ሠራተኞች በሥራ ላይ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ ይህንንም መረጃ ወር በገባ በ 20 ኛው ቀን የፋይናንስ ተግባርን ለሚያከናውነው የሥራ ክፍል ያሳውቃል፡፡ በግልባጩም የአስተዳደር ተግባርን ለሚያከናውነው የሥራ ክፍል ያሳውቃል በማለት ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በመመሪያው መሠረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

   ከቀን 7/7/2014 ጀምሮ ስራቸውን ለለቀቁ የመ/ቤቱ ሰራተኛ የሚያዝያ ወር ደመወዛቸው ብር 4,989.00 እንዲሁም የስነ ምግባር ፀረ ሙስና ዳሬክቶሬት ከቀን 10/7/14-16/7/14 ባዘጋጀው ስልጠና ላይ እንደተሳተፉ ተደርጎ ብር 3,213.00 አበል በድምሩ ብር **8,202.00** አለአግባብ የተከፈላቸው መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

2. በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀፅ 9 መሰረት ማንኛውም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ለክፍያዎች መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

   ከአገር ውጭ ለሚገኙ፤ የዐመት ፈቃድ ላይ ለነበሩ፤ በህመም ምክንያት በስራ ላልተገኙ እንዲሁም በሥራ ገበታቸው ላይ ላሉና ስራ ላይ መኖራቸው የሰዓት መቆጣጠሪያ ላይ ለፈረሙ ሰራተኞች፤ ስልጠናው የተሰጠበት ግዜ እና የሰዓት መቆጣጠሪያ ዝርዝር የቀረበበት ግዜ የማይመሳከር በመሆኑ እንዲሁም የሰዓት መቆጣጠሪያ ፊርማ ሳይቀርብ ለስልጠና አዳማ እንደሄዱ ተደርጎ በድምሩ ብር **563,949.00** አለአግባብ የውሎ አበል ተከፍሎ መገኘቱ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

3. የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈጸም ወጪው ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪዉን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪዉ በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ውስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈፀም እንደማይገባ መመሪያዉ ይገልፃል። ይሁን እንጂ
በቀን 26/01/2014 በወጪ ማስመስከሪያ ሰነድ ቁጥር 4779 በሂሳብ አርዕስት 2221101/ ክፍያ በ2013 በጀት ዓመት መከፈል የሚገባው የውሎ አበል ብር 13,770.00 ከበጀት ዓመቱ ውጭ ለ2014 በጀት ዓመት ከተፈቀደ በጀት ተከፍሎ ተገኝቷል።

4 የፌደራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል 5 አንቀጽ 17 ቁጥር 1 ላይ የፌደራል ዋና ኦዲተር፣ የመሥሪያ ቤቱ ኦዲተሮች ወይም የፌደራል ዋናው ኦዲተር ወኪሎች ለምርመራ ጠቃሚና አስፈላጊ የሚመስሏቸውን መጻሐፍት፣ መዝክሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶችና ሌሎች የጽሑፍና የቃል መረጃዎች ሁሉ ሲጠይቁ የተጠየቀው ግለሰብ፣ ሠራተኛ ወይም ባለሥልጣን በትክክልና በተሟላ አኳኋን ወዲያውኑ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት ይገልፃል። ይሁን እንጂ በድምሩ ብር 103,609.75 የተከፈለባቸው የወጪ ሰነዶቹ ለኦዲት እንዲቀርቡ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ሰነዶቹ ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም ።

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 4 ከተገለፁት በስተቀር የመ/ ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀም በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

<u>ህጋዊነትን ያልተከተሉ ጉዳዮች (Compliance Matters)</u>

<u>ገቢ፤</u>

5. የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር190/2002 ስለፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ክፍል 4.21.1 የመንግስት መ/ቤቶች ለሚያቀርቡት አገልግሎት አዲስ ተመን ወይም በነባር ዋጋ ላይ የሚደረግን ለውጥ በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሃሳብ በሚኒስትሩ በኩል ለሚኒስቴሮች ም/ቤት አቅርበው ማጸደቅ እንደሚኖርባቸው የተገለጸ ቢሆንም፤ ከቴያትር፣ ከፊልም ምርቃት፣ ከመጽሀፍት ምርቃት እና ከሌሎችም ምንጮች ለሚሰበስበው ገቢ

በሚመለከተው አካል ተመን ሳያስፀድቅ በድምሩ ብር **3,115,750.54** ገቢ መሰብሰቡ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

6. የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ16.26 ውል መፈረም ንዑስ አንቀጽ 16.27.4 በንዑስ አንቀጽ 16.27.3 መሰረት (ሽ) አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ገደብ ውስጥ ዕቃውን ባያስረክብ (ሀ) አቅራቢ ሳይፈፅም በቀረበው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 0.001 ወይም 1/1000 የጉዳት ካሳ መክፈል እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ለደንብ ልብስ የሚሆን ጨርቅ ግዥ ለመፈፀም ከሰይድና ሀናን የደንብ ልብስ ጋርመንት ጋር እንዲሁም አናሪያ ከተባለ የልብስ ስፌት ድርጅት ጋር ውል ቢገባም፤አቅራቢዎቹ በውላቸው በተገለፀው የማቅረቢያ ግዜ ባለማቅረባቸው በድምሩ ብር **11,199.08** የጉዳት ካሳ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

**<u>ተሰብሳቢ ሂሳብ፤</u>**

7. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት፤ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ፤ በሂሳብ መደብ (5217399) 4274 ለሌሎች ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ በሚል በተሰብሳቢ የተያዘ ብር **3,396,738.07** ከአንድ ዓመት በላይ ሳይወራረድ የቆየ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ በኦዲት ታውቋል፡፡

**<u>ተከፋይ ሂሳብ፤</u>**

8. በፌዴራል መንግስት መስረያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 5 በተመለከተው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱንና ቴአትር ቤቱ ተከፋይ ሂሣቦችን በገባው ግዴታ መሰረት በወቅቱ የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፦ በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር **304,349.58** በወቅቱ ለባለመብቱ ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ በኦዲት ታውቋል፡፡

**በጀት፤**

9. በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 መሠረት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ ሊያውሉ እንደሚገባቸው ይገልፃል፡፡ ሆኖም የመ/ቤቱ የ2014 ዓ.ም በጀት አጠቃቀም ሲገመገም ብር 88,957.49 ከተፈቀደው በጀት በላይ የወጣ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

**ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች(Emphasis matter)**

10. የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀፅ 9 መሰረት ማንኛውም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ለክፍያዎች መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ የተለያዩ ባለሙያዎች የተለያየ ቀን ትርኢት ላሳዩበት ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር 600.00 ለባለመብቱ ለመከፈሉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
11. የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ጥራዝ 2 የሂሳብ አወቃቀር ሥርዓት ወጪዎች በትክክለኛ የሂሳብ መደባቸውን ጠብቀው ተመዝግበው ሪፖርት መደረግ እንዳለባቸው በሚያዘው መሠረት መከናወኑ ኦዲት ሲደረግ፡ ለዲጂታል እስክሪን የማስታወቂያ ፈቃድ ማውጫ ለአዲስ አበባ መስተዳድር ብር 140,400.00 ሲከፈል ወጪው በሂሳብ አርዕስት ቁጥር 2241106(6256) መመዝገብ ሲገባው 2241109(6259) በውሃ መክፈያ  የሂሳብ አርእስት ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
12. በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 መሠረት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡ በሥራ ላይ ሊያውሉ እንደሚገባቸው ይገልፃል፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴያትር የ2014 በጀት አጠቃቀም ሁኔታ ሲገመገም ከ(10%) በላይ ያልተሠራበት በጀት ብር **12,774,358.73** መኖሩ  በኦዲት ታውቋል፡፡

**ሌሎች ጉዳዮች(Other matter)**

**የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና አጠባበቅ፣**

የመ/ቤቱ የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ዓመታዊ  ንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ከወጪ ቀሪው ያልተመሳከረ  መሆኑ፤

- የተለያዩ ዕቃዎች እና የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች  አገልግሎት ሳይሰጡ  ለረጅም ጊዜ የቆዩ  መሆኑ፤
- በርካታ የመኪና ተመላሽ እቃዎች እና በቁጥር 3 የመኪና ባትሪዎች ሳይወገዱ  የተገኘ መሆኑ ፤

**<u>የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ፣</u>**

ኮድ ኢት 4-16818 KUN 25 LPRMDHV መኪና ከ1ዓመት በላይ ለጥገና    ሞኤንኮ ጋራዥ መቆየቱን፤

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከሰላምታ ጋር

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት**